# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 230 ጥቅምት 1 2005 ገጽ 1


የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብጫ ካርድ በማሳየት ወያኔን “ሃይማኖታችንን እንወዳለን፤ ጣልቃ አትግባብን” ብለውታል። ኢትዮጵያዊያን ለእምነታችን ያለን ክብር በሰንደቅ ዓላማችን ውስጥም የሰፈረ ጉዳይ ነው። እላይ እንደተገለፀው ብጫ የሃይማኖት፣ የአበባና የፍሬ ምሳሌ ነው። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብጫ ወረቀት፣ ፊኛና ጨርቅ በማሳየት ለሃይማኖታቸው ያላቸውን ክብር በማሳየት ወያኔ ጣልቃ ገብነቱን እንዲያቆም ጠይቀዋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ በቆየባቸዉ አመታት ያከናውናቸው የነበሩት በርካታ ጉዳዮችን ለፓርቲውም ሆነ ለሚንስትሮች ምክር ቤትም ወይም ለይስሙላ ፓርላማ እንደማያሳውቅ ምንጮች አጋለጡ

ኢትዮጵያ አገራችንን ለ21 አመታት የገዛው ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ከፍተኛ በጀት የሚጠይቁ ትላልቅ ውሳኔዎችን በዙሪያው ላሰባሰባቸው የካቢኔ ምንስትሮችም ሆነ ለፓርላማው ሳያሳውቅ በራሱ ፈቃድ ብቻ ያስተላልፍና ያስፈጽም እንደነበረ ጉዳዩን በቅርበት ይከታተሉ ከነበሩ ሚንስተሮች የተገኘ መረጃ አጋለጠ።

መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ለማንም ሳያማክር በግል ሥልጣኑ አስጀምሮት ከነበሩ ፕሮጄክቶች አንዱ ለኤርትራ ተቃዋሚዎች ይሰጥ የነበረው የፋይናንስና የማቴሪያል እርዳታ እንደነበረ የገለጹ ምንጮች የርሱን መሞት ተከትሎ ተቃዋሚዎቹ ከፍተኛ ችግር እንደገጠማቸው ገልጸዋል።

የኤርትራን ተቃዋሚዎች ለማደራጀት መለስ ዜናዊ በግሉ ይዞት በነበረው ፕሮጄክት ባህር ዳር ከተማ ዉስጥ ተቃዋሚዎቹ ወደ ኤርትራ የሚያስተላለፉት የሬዲዮ ስርጭት በጥራት እንዲሰማ ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ የሬዲዮ ጣቢያ ግንባታ ስራ ከተጀመረ ቦኋላ ከዚህ አለም በሞት በመለየቱ ምክንያት የፕሮጀክቱ ባለቤቶች የሆኑት የኤርትራ መንግስት ተቃዋሚ ኃይሎች ግንባታው እንዲጠናቀቅላቸው ለመጠየቅ ከመለስ ዜናዊ ጋር በነበራቸው ቅርበት ስለፕሮጀክቱ ሊያውቁ ይችላሉ የተባሉትን የፍትህ ምንስትሩ ብርሃን ሃይሉን፤ የቀድሞ የአማራ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንትና የአሁኑ ምክትል ጠቅላይ ምንስቴርን ድመቀ መኮንንን፤ የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት አያለው ጎበዜን በየተራ ቢያነጋግሩም ጉዳዩን አውቃለሁ የሚል አንድም ባለሥልጣን እንዳልተገኘ የደረሰን መረጃ አጋልጦአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የወያኔ ፓርላማ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሹመት በቀረቡለት እጩዎች ማንነት ላይ ሲጨቃጨቅ መዋሉ ተዘገበ

ባለፉት ሃያ አመታት ዉስጥ አንድም ቀን የተቃዉሞ ድምጽ አሰምቶ የማያዉቀዉ የወያኔ ፓርላማ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ለሹመት በላካቸዉ ዳኞች የብሔር ስብጥር ላይ ቀኑን ሙሉ ሲጨቃጨቅ መዋሉ ብዙዎችን እንዳስገረመ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ዘገባ ገለጸ።

የወያኔ ፓርላማ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ መለስ ዜናዊ የላከለትን ሁሉ ያለምንም ክርክርና የሃሳብ ልዩነት ተቀብሎ ሲያጸድቅ እንደኖረ እየታወቀ ከሰሞኑ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ለሹመት የላካቸዉን ዳኞች የብሔር ስብጥር አስመልክቶ ያካሄደዉ የመረረ ክርክር መነሻው ምን እንደሆነ የህዝብ መነጋገሪያ ሆኖአል ያለው ዘጋቢያችን ከፓርላማው ውሎ ቦኋላ ያነጋገራቸው አንዳንድ የፓርላማዉ አባላት ሳይቀሩ በሁኔታው መገረማቸውን አክሎ ገልጾአል።

የአገሪቱ መከላከያ ሠራዊት አዛዥነት ቦታ ላይ ሲሰጡ የኖሩ ሹመቶችን፤ የካቢኔ ሚንስትሮችን ፤ አምባሳደሮችን የተለያየ የንግድና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ስልጣን እርከኖች ላይ የነበሩትን ሹመቶች አስመልክቶ አንድም አስተያየት ሰጥቶ የማያውቀው የወያኔ ፓርላማ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ለሹመት ባቀረባቸው 45 ዳኞች የብሄር ማንነት ላይ ሲነታረክ መዋሉ ምናልባትም አዲሱን ጠቅላይ ሚንስቴር ስልጣን ላለመቀበል ወይም ለመጋፋት የተወሰደ እርምጃ ሳይሆን አይቀርም የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች አሉ።

ያለፈው ሃሙሱን የፓርላማ ዉሎ በቅርብ የተከታተሉ ሰዎችን በይበልጥ ያስገረመዉ ፓርላማዉ አለልማዱ ሲከራከር መዋሉ ሳይሆን በትግራይ ልጅነት የተሰባሰቡ ጥቂት ስግብግብ ግለሰቦች ያሰኛቸዉን ሲሾሙና ሲሽልሙ ትንፋሽ ያልተነፈሰዉ ፓርላማ ዛሬ በጣት የሚቆጠሩ ዳኞች ሹመት የብሔር ስብጥር ሚዛናዊ አይደለም ማለቱ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ በየቦታዉ እየተዘዋወረ የህዝብ አስተያየት የሰበሰበዉ ዘጋቢያችን በላከልን ዜና ገለጾአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## በቱባው የወያኔ ካድሬ ዓባይ ጸሃዬ የሚመራ ቡድን በሟቹ ጳጳስ አቡነ ጳውሎስ ምትክ ሌላ የወያኔ ካድሬ ጳጳስ ለመሾም ሶስት እጩዎች ማቅረቡን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች እንዳገኘ ዘሀበሻ ዘገበ

እንደ ምንጮቹ መረጃ እጩ ጳጳሳቱ አቡነ ማቲያስና አቡነ ጎርጎሪዎስ ከትግራይ፣ አቡነ ገሪማ ከሸዋ ናቸው።

በዘመነ የቤተክርስቲያን አባትነታቸው ሙሉ አወዛጋቢ ሆነው የኖሩት አቡነ ማትያስ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት የፕትርክና ዘመን፣ መንበራቸውን በመተው የኢዲዩ አባል በመሆናቸውና በሌሎችም በርካታ ምክንያቶች ተወግዘው "አቡነ ማቲያስ" የሚለውን መጠሪያቸውን ተነጥቀው እንደነበር የውስጥ አዋቂዎቹ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከዚም ሌላ እኚሁ አቡነ ማቲያስ ቤተክርስቲያኒቱ ከሶስት ቦታ እንድትከፈል ምክንያት ከሆኑት መካከል ግንባር ቀደሙ ሲሆኑ በአሁኑ ሰአት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ናቸው - እንደ ምንጮቹ።

ሌላው እጩ አቡነ ጎርጎሪዎስ በአሁኑ ሰዓት የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሲሆኑ ለእጩነት የቀረቡት ከሟቹ አቡነ ጳውሎስ ጋር ባላቸው ቅርበትና ለወያኔ ስርዓት ባላቸው ታማኝነት መሆኑ ተገልጿል።

የመጨረሻው ከአቡነ ጳውሎስ ያልተናነሰ የማእረግ ስም ያላቸውና " ዶክተር አቡነ ገሪማ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዋና ጸሃፊ፣የቤተክርስቲያን የውጪ ግንኙነት ሃላፊ፣ የድሬደዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ" እየተባሉ የሚጠሩት ዋነኛው እጩ ናቸው።

በዓለማዊው ሹመት ሃይለማርያም ደሳለኝ የመለስን ሌጋሲ ለማስፈጸም እንደተመደበ ሁሉ እነኚህም
እጩዎች የአቡነ ጳውሎስን ሌጋሲ በማስፈጸም የወያኔን ስርዓት እንደሚያገለግሉ ታምኖባቸው የሚመደቡ ናቸው በማለት ሌሎች የቤተክርስቲያኒቱ አባቶች እየገለጿቸው እንደሆነ የምንጮቹ መረጃ ያሳያል።

በሌላ በኩል አቡነ ጳውሎስ ከሞቱ በኋላ በአቃቤ መንበርነት የተሾሙት አቡነ ናትናኤል ለአራተኛው ጳጳስ አቡነ መርቆሪዎስ" ይድረስ ለብጹእ ወቅዱስ ፓትሪያሪክ አቡነ መርቆሪዎስ ሊቃነ ጳጳሳት ዘ-ኢትዮጵያ" በማለት ደብዳቤ ከመጻፋቸውም በላይ በስደት የሚገኘው ሲኖዶስ ወደ ሀገር ቤት እንዲገባ መጠየቃቸውን በጎ ነው ያሉት የቤተክርስቲያኒቱ አባቶች አቡነ ናትናኤል፣ ፓትሪያሪክ በህይወት እያለ ሌላ መሾም የለበትም ከሚሉ ወገኖች ጎን መሆናቸውን ይናገራሉ።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ከቤተመንግሥት ላለመውጣት እያንገራገረች መሆኑ ተዘገበ

በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ እግር ለተተካው የወያኔ ጠቅላይ ሚንስትር ቤተመንግሥቱን እንድታስረክብ የተጠየቀቺው አዘብ መስፍን አስከዛሬ ድረስ ፈቃደኛ መሆን ባለመቻሏ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ቀድም ሲል ይኖርበት ከነበረበት ብስራተገብርዔል አካባቢ እየተመላለሰ ለመስራት መገደዱን ለማወቅ ተችሎአል።

አዘብ መስፍን ቤተመንግሥቱን የሙጥኝ ብላ አለቅም ያለቺበትን ምክንያት በቅርበት የሚያውቁ ምንጮች እንደገለጹት መለስ ዜናዊ በታዛዥነቱና በታማኝነቱ ለዚህ ሥልጣን ላበቃው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ለ21 አመታት የኖረችበትን ቤትና ግቢ ለቆ መውጣት እንደመደፈር ቆጥራ ነው።

የመለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት ተከትሎ ህወሃት ኢህአደግ ውስጥ በተፈጠረው ክፍፍል የአዘብ መስፍን አንጃ የሆኑት በረከት ስምን፤ ተፈራ ዋልዋና አዲሱ ለገሰ አዜብ ላልተወሰነ ጊዜ እዚያው ቤተመንግሥት ውስጥ እንድትቆይ ለሃይለማሪያም ደሳለኝ መመሪያ ሰጥተውታል ተብሎአል።

በዚህም ምክንያት ሃይለማሪያም ደሳለኝ " ተጠናቂቄ ወደ ቤተመንግሥት ልግባ" የሚል ጥያቄ እስከዛሬ እንዳላነሳ ነገር ግን ጠቅላይ ሚንስቴር ከሆነ ወዲህ በተመደበለት ልዩ ጥበቃና አጀብ ከሚኖርበት ሰፈር ወደ ሥራ ሲወጣና ሲገባ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ በመፈጠሩ የአካባቢው ህዝብ የተሰማውን ቅሬታ ለማርገብ ለቤተመንግሥቱ ቀረብ ያለ ቦታ እንዲሰጠው ይህ እስኪሆን ድረስ የጥበቃው ጋጋታ እንዲቀንስለት ሰሞኑን ለበረከት ስምን አቤት ማለቱን ታማኝ ምንጮች አያይዘው ገልጸዋል።

የሃይለማሪያም ደሳለኝን ከከተማ እየተመላለሰ መሥራት የታዘቡ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ከአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር በስተጀርባ ሥልጣንን የሚቆጣጠረው ህወሃት ግለሰቡን በመሳሪያነት (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ወያኔ የብጫ ትርጉም አይገባውም፤ ምሱ መገደድ አሊያም መወገድ ነው!!!

ዓርብ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለወያኔ አገዛዝ ብጫ ካርድ አሳዩ። ብጫ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ብዙ ትርጉሞችን ያለው ቀለም ነው።

1ኛ. ብጫ የሰንደቅ ዓላማችን ቀለም ነው። እንደሚታወቀው የሰንደቅ ዓላማችን ሶስቱ ቀለማት የየራሳቸው ምሳሌያዊ ትርጉም አላቸው። አረንጓዴው ተስፋ፣ ልምላሜና ሀብት፤ ብጫው ሃይማኖት፣ አበባና ፍሬ፤ ቀዩ ፍቅር፣ መሥዋዕትነትና ጀግንነትን ይወክላሉ።

2ኛ. በእግር ኳስ ጨዋታ ህግ ብጫ ማስጠንቀቂያ ነው። አንድ ተጫዎች የጨዋታ ህግ ክፉኛ ሲተላለፍ ብጫ ካርድ በመጨረሻ ማስጠንቀቂያነት ይሰጠዋል። ተጫዋቹ “ደግመህ ብታጠፋ ትባረራለህ” መባሉን አውቆ ህግን አክብሮ ተጠንቅቆ መጫወት ይጀምራል ደግሞ ካጠፋ ከጨዋታዉ እንደሚባረር ያውቃል።

3ኛ በትራፊክ ህግ ብጫ የአደጋ ማስጠንቀቂያ ምልክት ነው። ህግን የሚያከብር አሽከርካሪ ብጫ የትራፊክ ምልክት ሲያይ ራሱንም ሊሎችንም ከአደጋ ለመታደግ ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርጋል።

መስከረም 25 ቀን 2005 ዓም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብጫ ካርድ ማሳየታቸው ከላይ በዘረዘርናቸው ሶስቱ ትርጓሜዎች አንፃር ካየነው ትልቅ መልዕክት ያለው ተግባር ነው።

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብጫ ካርድ በማሳየት ወያኔን “ሃይማኖታችንን እንወዳለን፤ ጣልቃ አትግባብን” ብለውታል። ኢትዮጵያዊያን ለእምነታችን ያለን ክብር በሰንደቅ ዓላማችን ውስጥም የሰፈረ ጉዳይ ነው። እላይ እንደተገለፀው ብጫ የሃይማኖት፣ የአበባና የፍሬ ምሳሌ ነው። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብጫ ወረቀት፣ ፊኛና ጨርቅ በማሳየት ለሃይማኖታቸው ያላቸውን ክብር በማሳየት ወያኔ ጣልቃ ገብነቱን እንዲያቆም ጠይቀዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ብጫ የማስጠንቀቂያም ምልክት ነውና የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብጫ ካርድ በማሳየት ወያኔን “የምትሠራው ሥራ ህገወጥ ነው። ከዚህ ተግባር ታቀብ፤ አለበለዚያ ወዮልህ!” የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥተውታል። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብጫ ካርድ ሲያሳዩ “ወያኔ ሆይ በያዝከው መንገድ መጓዝ ከቀጠልክ በራስህም፣ በእኛም በአገራችንም ላይ አደጋ ይደርሳልና ታቀብ!” ማለታቸው ነው።

ዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ ግን ማሳሰቢያውንም ሆነ ማስጠንቀቂያውን አልተቀበለም። ወያኔ የሰንደቅ ዓላማችንን ክብር የሚያውቅ አይደለምና በብጫው ቀለም ስለተወከሉት ሃይማኖት፣ አበባና ፍሬ ደንታ የለውም። ወያኔ ለህግ የበላይነት ደንታ የለውምና ብጫ የማስጠንቀቂያ ካርድ ምኑም አይደለም። ወያኔ ለአገርና ሕዝብ ደህንነት ደንታ የለውምና እንኳንስ በብጫ ሊታቀብ ቀዩንም ቢሆን ጥሶ ያልፋል።

ወያኔ ማሳሰቢም ሆነ ማስጠንቀቂያ የማይገባው ግብዝ መሆኑ እሁድ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም. በግልጽ ታይቷል። አዛውንቶችንና ደካሞችን በማስገደድ ወደማይፈልጉት ምርጫ ሄደው በመራጮች መዝገብ ላይ እንዲፈርሙ አደርጓል። ወያኔ ግብዝ በመሆኑ ነው በትህትና የቀረበለትን አቤቱታና ማስጠንቀቂያ መቀበል ተስኖታል።

በወያኔ ግብዝ አስተሳሰብ መሠረት ለቴሌቪዥን ካሜራ የሚሞላ ሰው ከተገኘ በቂ ነው። ገለልተኛ ታዛቢ በሌለበት ቁጥሮችን መሙላት ቀላል ነው፤ ወያኔ ይህንን ከመፈፀም የሚያግደው ይሉኝታ አልፈጠረበትም። እሁድ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓም የተደረገው ይህ ነው። ጥቂት ሰዎች ተገደው ወጡ፤ የብዙ ሰዎች ስም መዝገብ ላይ ሠፈረ።

በመሠረቱ በወያኔ የተስተናገዱ ምርጫዎች ሁሉ እንደዚሁ ነበሩ። ወያኔ ጥቂትም ቢሆን የተቸገረው በ1997 ምርጫ ብቻ ነበር፤ ያኔም ቢሆን ችግር ገጥሞት የነበረው ታዛቢዎች በርከት ባሉባቸው ከተሞች ውስጥ ብቻ ነበር።

ለወደፊቱም ወያኔ ምርጫ እንዲያስተባብር ከተፈቀደለት የሚያደርገው ይህንኑ ነው። በምርጫ ማጭበርበር የወያኔ ተፈጥሮዓዊ ባህርይ ነው።

አንደኛ ዓመቱን ሊያከብር የተቃረበው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ በርካታ አዳዲስ ነገሮችን አሳይቶናል። የዓርብ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.ቱ የብጫ ካርድ ማሳየት ሥነሥርዓት በመልዕክቱ ይዘትም ሆነ በአደረጃጀቱ ታሪካዊ ለመባል የሚበቃ ነው።

ሆኖም ግን ወያኔ ብጫ ቀለም የሚያይበት ዓይን የለውም። ወያኔ የሕዝብን ጩኸት የሚሰማበት ጆሮ የለውም። ለሁላችንም የሚበጀው ወያኔን ማስገደድ ወይም ማስወገድ የምንችልበት አቅምና መንገድ ማዘጋጀት ነው። ለዚህ ታላቅ ግብ ጠንክረን እንሥራ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

.....................................................................................................................

## የአባይ ግድብ ጉዳይ የብዙዎችን ኪስ እያራቆተ ቢሆን ስለፕሮጀክቱ የሚያውቅ ግን እስካሁን አልተገኘም ተባለ

የአባይ ግድብ ጉዳይ የብዙ ኢትዮጵያዊያንን ልብ እንደሰቀለ የዚያኑ ያህል ደግሞ የብዙዎችን ኪስ እንዳራቆተ በስፋት እየተነገረ ባለበት በአሁኑ ሰዓት “ ከድሃ ገበሬ የእለት ጉርስ እየተቀነሰ ገንዘብ እየተሰበሰበለት ያለው ግድብ ከወሬ ያለፈ በዝርዝር የተጠና ፕሮጀክት አለው ወይ?” ብሎ ለሚጠይቅ ዛሬም አጥጋቢ ምላሽ መስጠት እንደማይቻል ሪፓርተራችን ያደረገው አጭር ዳሰሳ አመለከተ። የግንቦት 7 ድምጽ ሪፓርተር ይህን በተመለከተ ለጉዳዩ ቅርበት አላቸው የሚባሉ ባለሙያዎችን በማነጋገር የደረሰበትን እንደሚከተለው አቅርቦታል።

ሪፓርቱን ለማጠናከር ለተባበሩን ዜጎች ደህንነት ሲባል ስማቸውን ቀይረን አቶ መካሻ ያልናቸው ባለሙያ በውሃዎች ልማት ሚኒስቴር ውስጥ የአባይ ተፋሰስ ፕሮጀት ሠራተኛ ናቸው። ከአባይ ተፋሰስ ጋር በተያያዙ ፕሮጀክቶች ከ10 ዓመት በላይ ሠርተዋል። ሪፓርተራችን ስለህዳሴ ግድብ የሚያውቁት እንዲነግሩን ሲጠይቃቸው “ስለ አባይ በተለያዩ ደረጃዎች የተደረጉ ጥናቶች መኖራቸው አውቃለሁ። ከእነዚህ ጥናቶች ውስጥ ሚሊኒዬም ወይም ህዳሴ ግድብ የትኛው እንደሆነ ግን እኔም አላውቀውም” ብለዋል።

እርስዎ በአባይ ላይ የሚሠሩ ባለሙያ ካላወቁ ማን ያውቃል? ለሚለው ተከታይ ጥያቄ “ማን እንደሚያቅ አላውቅም። እውነቱን ለመናገር የሚያውቅ ሰው ያለም አይመስለኝም። ለምሳሌ የቤት ሥራ መሃንዲስ ነህ እንበል። የተለያዩ ቦታዎችን ለቤት ሥራ ያመቹ እንደሆነ እንድታጠና ትታዘዛለህ። እዚህ ቦታ እንዲህ ዓይነት፤ እዚያ ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ ቤት መሥራት ይችላል ብለህ ንድፍ ታቀርባለህ። እኔ አንዲህ አይነት ንድፎችን ብዙ አውቃለሁ። እነዚህ ግን የግድብ ፕሮጀክት ናቸው ማለት አይደለም። እነዚህ ከምልከታ ያላለፉ ጥናቶች ናቸው። እስከዛሬ ድረስ እስከመጨረሻው በዝርዝር የተጠና የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት አላየሁም” ሲሉ መልሰዋል። ሪፓርተራችን “በየቢል ቦርዱ ተለጥፎ የሚታየው ግድብ ምንድነው?” ብሎ በጠየቀ ጊዜ ምላሻቸው ሳቅ ነበር። በሳቃቸው መሃልም ይህንን ምስል “ኢንቴርኔት ጎጎል ውስጥ ብትፈልግ ታገኘዋለህ። ዘንድሮ የስዕል ችግር የለም” ብለውታል።

ከዚህ በኋላ ሪፓርተራችን የግብርና እንዲሁም የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ባለሙያዎችን ለማነጋገር ሞክሮ ተሳክቶለታል። ሆኖም ግን የህዳሴ ግድብን ዝርዝር ጥናት አይቻለሁ የሚል ባለሙያ አላገኘም።

አቶ ሙክታር ዓለም ባንክ ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያ ናቸው “ስለ ህዳሴ ግድብ እቅድ የማይታወቀው በከፍተኛ ሚስጢር ስለተያዘ ይሆን?” ተብለው ሲጠየቁ “እኔ እንደሚመስለኝ ፕሮጀክቱ ሚስጢራዊ ያደረገው ከመጀመሪያው የሌለ በመሆኑ ነው” ብለዋል። አያይዘውም “ይህ ምስጢራዊ ያልከው ፕሮጀክት ያሞኘው ኢትዮጵያዊያንን ብቻ አይደለም። ግብፅና ሱዳንም ድንገት ይኸ ነገር እውነት ቢሆንስ የሚል ስጋት ውስጥ ገብተዋል። አንድ ልብ ወለድ ፕሮጀክት ተጨባጭ ስጋት ሲፈጥር ሳይ ይህ የመጀመሪያዬ ነው” ብለዋል።

ሪፓርተራችን ያነጋገራቸው ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ መጠቀም አለባት ብለው ያምናሉ። ሆኖም ግን በሚገባ የተጠና ፕሮጀክት ሊኖር እንደሚገባ ያሰምሩበታል። በእነሱ እምነት አሁን በዚህ ደረጃ የተጠና ፕሮጀክት የለም። በአንድ ወቅት የሕዝብን ትኩረት ለመሳብ ተብሎ የተነገረ የልብ ወለድ ፕሮጀክት ጥሩ የፕሮፖጋንዳ መሣሪያ እና የገንዘብ መሰብሰቢያ ሆኗል ብለው ያምናሉ።

በአባይ ጉዳይ ግብፅና ሱዳን ስጋት ውስጥ የገቡ ይመስላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ የተስፋ ዳቦ እየገመጠ የእለት ጉርሱን ሳይቀር ለአባይ እየገበረ ነው።

## የወያኔ ፓርላማ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሹመት በቀረቡለት እጩዎች ማንነት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በተለይ አንድ በቅርቡ ከመከላከያ ሠራዊት የተሰናበቱ ከፍተኛ መኮንን ለዘጋቢያችን በሰጡት ቃል በቅርቡ ፓርላመዉ ባልተሰበሰበበትና አገሪቱን የሚመራ ጠ/ሚኒስትር በሌለበት ቦታ ከ38 ተሿሚ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ዉስጥ ለ25 የትግራይ መኮንኖች የተሰጠዉን አጠያያቂ ሹመት ጉዳይ መመልከት ያልፈለገዉ ፓርላማ በዳኞች ሹመት ጉዳይ ሲከራከር መዋሉ እጅግ እንዳሳዛናቸዉ ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ዉስጥ የመከላከያ ሠራዊቱ፤ የፖለስ ሠራዊትና የድህንነት መስሪያ ቤት በመለስ ዜናዊ ግዜም ሆነ ዛሬ ሙሉ በሙሉ የሚመራዉ በትግራይ ተወላጆች መሆኑን የግንቦት ሰባት ድምጽ በተደጋጋሚ መዘገቡ አይዘነጋም።

## ይድረስ ለኢህአደግ መከላኪያ ሠራዊት አባላት በሙሉ !!!

በአንድ ወቅት መለስ ዜናዊ ድርጅታችን በስብሷል ብሎ ነበር። ይሄ እውነት ነው። ህወሃት/ኢሕ አዴግ ከመበስበስ በላይ ሁኗል። የበሰበሰ የሚያሰኘውም በህወሃት መሪነትና አስተማሪነት ድርጅቱ የተዘፈቀበት የዝሪፊያ ማእበል ነው። እነዚህ ዘረኞች የባእድ አገር የያዙ ይመስል በሁሉም አቅጣጫ በዝርፊያ ባህር ውስጥ እየዋኙ ነው። በዝርፊያቸው ጥልቅትና ስፋት የሚተካከላቸው ባለመገኘቱም በዚያች አገር ሚሊየነሮቹ እነርሱ ሆነው ሌላው እነርሱ ካልፈቀዱለት መኖር እማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ዛሬ ሿሚና ሻሪ፤ ሰጪና ከልካይ እነዚሁ ዘረኞችና ዘራፊዎች ናቸው። እነዚህ ጥቂት ዘረኞች ትግራይን ነፃ እናወጣለን ብለው ከተነሱ እለት ጀምረው በውል የሚታወቁበት በነፍስ ግዲያና በዝሪፊያ ነው። ህወሃቶች ሳይገድሉ መኖር፤ ሳይዘርፉ ባለፀጋ መሆን እንደሚቻል አያውቁም። ከዚህ ነውር ተግባሮቻቸው ተላቀውም ወደ በጎ ሂሊና መመለስ የማይችሉበት ደረጃ ላይ በመድረሳቸውም መሪያቸው በስብሰናል ብሎ እንዲናገር ግድ ሆኖበት ነበር። ህወሃት/ኢሕአዴግ በስብሷል ሲባል ወደ በጎ ሂሊና ተመልሶ ከሌሎች ጋር በሰላም ሊኖር የሚችልበትን ግዜና ሁኔታ አልፏል ማለት ነው። ይሄም ማለት ከገባበት ጥልቅ የዝሪፊያ ማእበል እና ከታሠረበት ዘረኛ ሰንሰለት በልመናም ሆነ በሽምግልና መውጣት አይችልም ማለት ነው።

እንደሚታወቀው ህወሃቶች የሚዋኙበት የዝርፊያ ባህር እንደ ውቂያኖስ ጥልቅና ሠፊ ነው። የዘረጉትም የነፍስ ግዲያ መረብ የህልውናቸው መሠረት ሁኗል። ይህን የህልውናቸውን መሠረት ሠብረው፤ እንደ ውቂያኖስ ጥልቅና ሠፊ ከሆነው የዝሪፊያ ባህር እንዲወጡ ማስገደድ ግዜው የሚጠይቀው ትክክለኛ ተግባር ነው። እነዚህ ነፍሰ ገዳዮችና ዘራፊዎች በፈቃዳቸው ከገቡበት የዝሪፊያ ባህር ውስጥ ወጥተው ነፃነት ወዳለበት መጥተው እርቅ ያደርጋሉ ብሎ መጠበቅ ማለት "እባብ ሆይ እርግብ ሁኝሊኝ" እንደ ማለት ይቆጠራል። ህወሃት ወደ እርቅ አይመጣም። ህወሃት በዚያች አገር ህዝቡ የሚፈልገው የህግ የበላይነት ሠፍኖ ሠላም እንዲሆን ምንም ፍላጎት የለውም።

እነዚህ ነፍሰ ገዳዮችና በዝሪፊያ ማዕበል ውስጥ የሚዋኙ ብድኖች ከሰሞኑ የኢትዮጵያን መከላከያ ኃይል ሰብስበው ሲገመግሙ ከርመዋል። የግምገማቸው ማሠሪያ ሃሳብ *"በመሃላችን ጠላት ገብቷል፤ ይህን ጠላት ካላወጣችሁ እንደ ደርግ ወታደር ለማኝ ሁናችሁ ትቀራላችሁ"* የሚል ነው። ህወሃቶች ክፋታቸው የፈጠረባቸውን ፍርሃት ድሃው ወታደረም አብሯቸው እንዲፈራላቸው እየወተወቱ ነው። ህወሃት የቀደሞውን የአገሪቷን መከላከያ ኃይል በትኖ ሜዳ ላይ በመጣሉ ወታደሩ ለመለመን መገደዱ የሚታወስ ነው። ህወሃት የሚያስበው በራሱ የአስተሳሰብ ደረጃ ስለሆነ እርሱ ያደረገውን ነውር ነገር ሁሉም የሚያደርገው ይመስለዋል። እነዚህ ቡድኖች ነውርን ከደጉ መለየት የማይችሉ የጨካኝ ግለሰቦች ስብስብ መሆኑን ተግባሮቻቸው ሁሉ ህያዋን ምስክሮች ናቸው። በአሁን ሠዓት ነፃነት ይሁን፤ ፍትህ ይንገስ፤ እውነተና ዴሞክራሲ ይምጣ እያሉ ትግል የጀመሩ ኃይሎች ለአገሪቷ ዘላቂ ጥቅም እና ሠላም የሚሠሩ እንጂ እንደ ህወሃት ደምና አጥንት እየቆጠሩ ለበቀል የተዘጋጁ አይደሉም።

ህወሃቶች እንደሚሉት አሁን ባለው መከላከያ ውስጥ ጠላት መግባቱ ሃሰት አይደለም። ይህም ጠላት "እውነት" ይባላል። እውነቱ - ደግሞ ህወሃት የእኔ ናቸው ብሎ የሾማቸው ካርታ ይዘው የቆሙበትን ቦታ ለማሳየት እንኳ ብርቱ ችግር ያለባቸው ጄኔራል ተብየዎች ከድሃው ህዝብ ላይ ዘርፈው ተንደላቀው ሲኖሩ የድሃው ልጅ ወታደር ግን ከነ ዘመድ አዝማዶቹ የጥቂት ጄኔራሎችና ወዳጆቻቸው አናኗሪ ሁነው መቅረታቸው ነው። እውነቱ - ጄኔራሎቹ ከህግ በላይ ሁነው በአንድ በኩል ነጋዴዎች በሌላ በኩል ደግሞ የጦር አበጋዞች ሁነው የፈለጉትን አድርገው ሲኖሩ ወታደሩ ግን ሳያውቀው የእነርሱ ወንጀል ተከላካይ ሁኖ መኖሩ ነው። እውነቱ - ጄኔራሎቹ ከድሃው ህዝብ ላይ የዘረፉት ሃብት ለዘመድ አዝማዶቻቸው ተከፋፍሎ ባለ ብዙ ሃብት ባለቤት እንዲሆኑ ሲደረግ የወታደሩ ዘመዶች በርሃብ አለንጋ የሚገረፉ መሆናቸው ነው።

ዋናው እውነት ግን ህወሃት/ኢሕአዴግ ከያዘው ስልጣን ቢወርድ ወታደሩ የሚጎድልበት አንዳችም ነገር አለመኖሩ ነው። ይልቁንስ ህወሃት/ኢሕአዴግ ቢወገድ ወታደሩ ከአንድ ዘረኛ ድርጅት ጥቅም አስጠባቂነት ወጥቶ ለአገሩ ልዕልናና ለዜጎቹም ጋሻ መከታ የሆነ መከላከያ ኃይል መሆን በቻለ ነበር ። ህወሃት ባይኖር ኑሮ በየሜዳው እየወደቀ ተረስቶ የሚቅር ወታደር አስታዋሽ ኑሮት ከወገኖቹ የሚገባውን ክብርና ሞገስ ባገኘ ነበር። ህወሃት ባይኖር ኑሮ በሠላም አስከባሪ ሥም በየባእድ አገራት ዘምቶ ሲያበቃ በስሙ የተገኘውን ገንዘብ የህወሃት የጦር አበጋዞች እርስ በርሳቸው ተከፋፍለው አንቱ የተባሉ ቱጃሮች ሆነው የፈለጉትን የሚጠግኑ፤የጠሉትን የሚሰብሩ ሁነው ቁጭ ባላሉ ነበር። ህወሃት ባይኖር ኑሮ በሶማሊያ ጎዳና ላይ አስከሬኑ የተጎተተው ያ ኢትዮጵያዊ ማን መሆኑን ባወቅነውና ያለ ጧሪ የቀሩ ዘመዶቹ የሚገባቸውን ክብር ማግኘት በቻሉ ነበር። ህወሃት በመኖሩ ወታደሩ ያተረፈው አንዳችም ጥቅም የለም። ለራሱ ማረፊያ አጥቶ ለዘመዶቹም ጋሻ መከታ መሆን አቅቶት በሰቀቀን ለመኖር ከመገደድ በቀር ያተረፈው ሌላ ነገር የሌለው የህወሃት / ኢህአደግ ወታደር የመኖር ህልውናው ከድርጅቱ መኖር አለመኖር ጋር የሚያስተሳስረው ምንም ነገር አይኖርም።

እንዲያውም ህወሃት ከያዘው ስልጣን ቢወርድ ወታደሩ ከዘረኛ እና አድሎዋዊ አስተዳደር ነጻ በመውጣት እስከዛሬ በቃል እንጂ በተግባር አይቶት ያማያውቀው መብትና ጥቅም ባለቤት ይሆናል እንጂ የሚጎድልበት አንዳችም ጥቅም የለም። ህወሃት ከስልጣን ቢወርድ ቀን ከለሊት እየተዘረፈች ያለች አገር እና በችጋር እየተሰቃየ ያለው ህዝብ እፎይ ይላሉ እንጂ በተራው ወታደር ላይ የሚደርስ አንዳችም ክፉ ነገር አይኖርም። ወታደሩን "እኛ ከሌለን ለማኝ ትሆናለህ" በማለት ዘረኛና ዘራፊ አልቆቹ ሊያስፈራሩት የሚሞክሩት ወታደሩን ተገን አድርገው የሚያካሂዱት ዝሪፊያ የሚያበቃ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በነፍስ ግድያና በዝሪፊያ እጃቸው ተይዞ በስልጣን ዘመናቸው ባዋረዱት ፍርድ ቤት ፊት ለፊት እንደሚገተሩ ስለሚያዉቁ ነው። ወታደሩና ወያኔ ውስጥ ያለው የበታች መኮንን ሁሉ አገራችን ውስጥ እየተካሄደ ያለው ትግል ፍትህ እኩልነትና የህግ የበላይነት የሚሰፍንበትን ሥርዓት ለመገንባት እንጂ በበቀልና በጥላቻ ስሜት እርሱን ከስራው አፈንቅሎ ለማኝ ለማድረግና ዘረኞቹ በቀድሞው አገር መከላኪያ ሠራዊት ላይ የወሰዱትን አይነት ኢፍትሃዊ እርምጃ በመውሰድ ዜጎችን ለሥራ አጥነት መዳረግ እንዳልሆነ ጠንቅቆ ይረዳል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ወታደሩ በዘሩና በፖለቲካ እምነቱ ምክንያት እየደረሰበት ያለውን አድሎና በአለቆቹ የሚካሄደውን ዝሪፊያ ስለሚያውቀው የህወሃት ጄኔራሎች የሚነዙትን የፈጠራ ሽብር እንደማይጋሯቸው እውነት ግድ ትለዋለች። በህወሃት ከሥልጣን መወገድ ሊፈሩ የሚገባቸውና ቀን የሚጎድልባቸው ዘርፈው ሚሊነየር የሆኑት፤ንጹሃን ዜጎችን ገድለው የጀገኑ የመሠላቸው እነዚያ ጥቂቶች እንጂ ድሃው ወታደር ሊሆን አይገባም።

ድርጅታችን ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ሌቦችን ከንጹሃን ይለያል። አገራችንን የበደሏትም ያዋረዷትም ጥቂቶች ደምና አጥንታቸውን ቆጥረው የተደራጁ መሆናቸውን ጠንቅቆ ይረዳል። ብዙሃኑ ጭቁን ወታደር የአድልዎና የበደሉ ገፈት ቀማሽ እንጂ በምንም መስፈርት የገዢዎቹ አካል ተደርጎ ሊቆጠሩ ይገባል ብሎ አያምንም። ስለዚህ ጭቁን ወታደሮች ከጥቂት ዘረኞችና ዘራፊዎች መረብ ራሳችሁን አላቃችሁ ለፍትህ፤ ለነፃነት እና ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ግንባታ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ ለማበርከት የምትችሉትን ሁሉ እንድታደርጉ ጥሪያችንን እናቀርብላችኋለን። ህወሃት/ ኢሕአዴግ በስብሷል። መበስበሱንም በመሪው አንደበት አውጆአል። እናም ደግመን ደጋግመን የምናቀርብላችሁ ጥሪ እናንተ የህዝብ ወገን የሆናችሁ ብዙሃን ወታደሮች ሆይ፤ ከበሰበሰ ስፍራ ምን ታደርጋላችሁ? ኑና ዛሬውኑ የነጻነት ትግሉን ተቀላቀሉ፤ እንዲህም በማድረጋችሁ ከሂሊናና ከታሪክ ተወቃሽነት ራሳችሁን ነጻ ታወጣላችሁ የሚል ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ከቤተመንግሥት ላለመውጣት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ብቻ ሊገለገልበት ሲል ነው የሾመው በማለት ጉዳዩን መነጋገሪያ እንዳደረገው ታውቆአል።

ይህ በዚህ እንዳለ ሰንደቅ የተባለው ጋዜጣ አዜብ መስፍን ቤተመንግሥቱን ለተተኪው ጠቅላይ ሚንስትር ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆኗ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአታል ሲል የዘገበ ሲሆን ማስጠንቀቂያው በማን እንደተሰጠና በማስጠንቀቂያው መሰረት ርክክቡ ባይፈጸም ምን እርምጃ ሊወሰድ እንደሚችል ወይም ለአፈጻጸሙ የጊዜ ገደብ ይኑር አይኑር የገለጸው ነገር የለም።

ጋዜጣው አክሎም ሶስት መኖሪያ ቤቶች በተለዋጭነት ለአዘብ እንደተዘጋጀላት አንዱን መርጣ እንዲትገባበት ቢነገራትም ባልታወቀ ምክንያት ቤቶቹን ለማየት እንኳን ፍቃደኛ እንዳልሆነች ገልጾአል።

የሰንደቅ ጋዜጣን ዘገባ ዋቢ በማድረግ ተሰጣት ስለተባለው ማስጠንቀቂያ ከምንጮቻችን ለማጣራት ሞክረን በዙሪያዋ ባሉ ቱባ ቱባ ወያኔ ባለሥልጣናት ድጋፍ ማንንም ከመጠፍ ለማትቆጥር አዜብ ማስጠንቀቂያውን ሊሰጣት ማን እንደሚችል ጥያቄ እንደሚፈጥርባቸው ገልጸው ሆኖም ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በባላንጣነት የሚያይዋት የአቦስብሃት ቡድን ተገፍትራ ከቤተመንግሥቱ እንድተወጣ የማየት ጉጉቱ ቢኖራቸውም ተሰጣት የተባለውን አይነት ማስጠንቀቂያ የመስጠቱ ድፍረትም ሆነ ብቃት የላቸውም ብለዋል።

## መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ በቆየባቸዉ አመታት ያከናውናቸው የነበሩት በርካታ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ከሁሉም የሚገርመው ስለጉዳዩ ያውቃሉ ተብለው ከተጠየቁት መካከል ምክትል ጠቅላይ ምንስትር ሆኖ የተሾመው የትምህርት ሚኒስትሩ ደመቀ መኮንን ጭራሹን የኤርትራ ተቃዋሚ አዲስ አበባ ዉስጥ መኖሩንም ሰምቶ እንደማያዉቅ በመናገር እርዳታ ፈላጊዎቹን አስደንግጦአል።

በቅርቡ ጠ/ሚኒስትር ሆኖ የተሾመዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ፓርቲዉ ኢህአዴግ የረጂም ግዜ የጋራ አመራር ልምድ አለዉ ብሎ ሲናገር የተደመጠ ቢሆንም እሱ እራሱ የአገሪቱ ምክትል ጠ/ሚኒስትር ሆኖ በቆየባቸዉ ሁለት አመታት ዉስጥ ዉሳኔያቸዉንም ሆነ አፈጻጸማቸዉን በፍጹም የማያዉቃቸዉን አያሌ ዉሳኔዎች መለስ ዜናዊ ብቻዉን ይወስን እንደነበር እነዚሁ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ገልጸዉ እንደዚህ አይነት ሀላፊነት የጎደላቸዉና አገርን ለችግር የሚያጋልጡ የመለስ ዜናዊ ስራዎች ከአሁን በኋላ በስፋት ለህዝብ ይፋ ሊሆኑ እንደሚችሉ ጠቁመዋል። ................................................................................

## የአሜሪካ ውጪ ጉዳይ ምንስትር የተሳተፈበት "ኢትዮጵያን ዲሞክራሲያዊ ማድርግ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ የአንድ ቀን ኮንፍረንስ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ መካሄዱ ታወቀ

ናሽናል እንዶዉመንት ፎር ዲሞክራሲ በመባል የሚታወቀዉና አሜሪካ ዉስጥ የሚገኘዉ የዲሞክራሲ ማስፋፊያና ተሟጋች አለም አቀፍ ተቋም ኢትዮጵያን አስመልክቶ ያዘጋጀዉ የግማሽ ቀን ኮንፍራንስ ዋሺንግተን ዲስ ዉስጥ ባለፈዉ ማክሰኞ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓም መካሄዱን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ዘገባ ገለጸ።

በኮንፍራንሱ ላይ ወያኔ በአገራችን ላይ የሚፈጽመው ሰቆቃ ሰለባ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና በአገራቸው ፍትህ ፤ እኩልነትና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የሚታገሉ በርካታ ዜጎች ተገኝተው እንደነበረ ዘገባው አመልክቶአል።

8 ሰዎች በሦስት ቡድን ተከፋፍለዉ ባቀረቡት ጥናታዊ መረጃ መነሻነት በተካሄደዉ በዚህ ኮንፍራንስ ላይ ፕሮፌሰር ብርሀኑ መንግስቱ፤ ወይዘሮ ማህደረ ጳዉሎስ እና አለም አቀፍ ሽልማት ተሸላሚዉ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ በመገኘት ያዘጋጁትን ጥናታዊ ስራ ያቀረቡ ሲሆን ሦስቱም ኢትዮጵዉያን የወያኔ አገዛዝና ዲሞክራሲ በፍጹም እንደማይተዋወቁ በመረጃ በማስደገፍ ለኮንፍራንሱ ተካፋዮች አስረድተዋል። ፓናሊስቶቹ ወያኔ በህዝባችን ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃና የሙብት ጥሰት በስፋት በማስረዳት በምንም መመዘኛ ተቀባይነት በሌለው መልኩ ዲሞክራሲን አፍኖ የኢትዮጵያን ህዝብ ሰብዓዊ መብቶች መርገጥ የቻለዉ በአሜሪካና በአዉሮፓዉያን ደጋፊዎቹ እርዳታና እይዞህ ባይነት መሆኑን በግልጽ አስረድተዋል።

ከላይ ስማቸዉ ከተጠቀሰዉ ሦስት ኢትዮጵያዉያን ዉጭ ሌሎች አምስት አሜሪካዉያን ተመራማሪዎች፤ የኮንግሬስ አማካሪዎችና የአሜሪካ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር ከፍተኛ ተወካዮችም ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው አገዛዝ ያላቸውን አስተያየት አቅርበዋል። ከእነዚህ ዉስጥ በተለይ አምባሳደር ዴቭድ ሽንና የዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር ተወካይዋ ካረን ሃንራሃም ያቀረቡትን አስተያየት የኮንፍራንሱ ተሳታፊዎች በከፈተኛ ደረጃ የተቃወሙ ሲሆን በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ መልስ እስኪያጥራቸው ድረስ ሲያፋጥጡዋቸው ውለዋል።

የወያኔን አፈናና ጭቆና ለማስተባበል በኮንፍራንሱ ላይ ተገኝቶ የነበረ አንድ የወያኔ ኤምባሲ ባልደረባ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ሃሳብን በነጻነት መግለጽ አስመልክቶ የሰጠውን አስተያየት በመቃወም በጋዜጠኝነት ሥም ተቃውሞ የሚያሰሙ የቀድሞ የደርግ ዜጠኞች የነበሩ ናቸው በማለቱ ወያኔ ሥልጣን ስይዝ ገና የ9 አመት ታዳጊ የነበረ ዳዊት ከበደ በምን ተአምር የደርግ ጋዜጠኛ ሊሆን እንደቻለ አሜሪካዉያን ጭምር ከማስገረም አልፎ አስቆአል።

## ኦህዴድ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩ ጁነዲን ሳዶ ከድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ተወግዶ ተራ አባል እንዲሆን ወሰነ። የመከሰስ መብቱም ሊገፈፍ እንደሆነ ተዘገበ

በተለያየ ጥቅማጥቅሞች ዜጎችን ደልሎ እንዳሻው ከተጠቀመባቸዉ በኋላ እንደቆሻሻ ወደ ዉጭ እያወጣ የሚጥለዉ የወያኔ ስርአት በቅርቡ በተለያዩ የስርአቱ የመገኛ አዉታሮች ስሙ በተደጋጋሚ ሲነሳ የሰነበተዉንና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር የሆነውን ጁነዲን ሳዶን ከኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነቱ ማስወገዱን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ሪፖርት ገለጸ።

ባለቤቱ ከሳዑዲ ኤምባሲ በተቀበለቺው የ50ሺ ብር ጉዳይና በወላጅ እናቱ መሬት ላይ በሚያሰራዉ መስጂድ ምክንያት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአገዛዙ ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ የገባው ጁነዲን ሳዶ ከወያኔ ጋር እጅና ጓንት በመሆን ለአመታት የገዛ ህዝቡን ስቃይና መከራ ሲያራዝም ከኖረ ቦኋላ የውንጀላ ክስ ተቀነባብሮበት በግምገማ ከኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነቱ ተወግዶ ለረጂም ግዜ በከፍተኛ መሪነት ባገለገለበት ድርጅት ዉስጥ ተራ አባል ሆኖ እንዲቀጥል ተወስኖበታል።
ጁኔዲን ሳዶ የወያኔ አለቆቹ ከኦህዴድ ምስረታ ጀምሮ የሚያሳዩትን የበላይነት ላለመቀበልና ድርጅቱን ከወያኔ ጥገኛነት ለማላቀቅ የተቃውሞ ድምጹን በየመድረኩ ማሰማት በመጀመሩ አቋሙ እንዳልተወደደለት የሚናገሩ ምንጮች ህወሃቶች ሌሎችን በሙስናና በሃብት ዘረፋ ወንጀል ለማሸማቀቅ የሚሰነዝሩትን ነቀፋ በመመከት እናንተስ ይህን ሁሉ ሃብት ከየት ይዛችሁ የመጣችሁ ይመስላችኋላ በማለት እንደሚጋፈጣቸው ይናገራሉ።

ኦህዴድ ውስጥ በተፈጠረው ግምገማ ምክንያት መለስ ዜናዊን በመተካት ጠ/ሚኒስተር ሆኖ የተሾመዉ ሀ/ማሪያም ደሳለኝ የሚመሰረተዉ ካቢኔ ጁነዲን ሳዶን እንደማያጠቃልል ከወዲሁ የታወቀ ሲሆን ከፓርቲዉ ማዕከላዊ ኮሚቴ የተባረረዉንና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትርነቱን ስፍራም በቅርቡ የሚለቀዉን የጁነዲን ሳዶን የወደፊት እድል ማወቅ አስቸጋሪ ሆኖአል ተብሎአል። ምክንያት ከፓርቲው ማ ዕከላዊ ኮሚቴ ሃላፊነቱ እንዲነሳ ሲወሰንበት ያለመከሰሰ መብቱም አብሮ እንዲነሳ ውሳኔ በመተላለፉ::
ለሪፖርተራችን አስተያይታቸውን የሰጡ አንድ የኦህዴድ አመራር አባል ሃይለማሪያም ደሳለኝንና ደመቀ መኮንንን በጠቅላይ ሚንስትርነትና በምክትል ጠቅላይ ሚንስትርነት ለማሾም በተደረገው የኢህሃደግ ስብሰባ ላይ ኦህዴድ ምንም እጩ እንዲያቀርብ አለመደረጉና ድምጽ አልባ ሆኖ መታለፉ ብዙዎችን እንዳስከፋ በዚህም ምክንያት ጁነዲን ሳዶ ኩርፊያው በግልጽ ከታወቀባቸው እንዱ በመሆኑ በሚቀጥለውየኢህአደግ ስብሰባ ድርጅቱን በመወከል ወደ ኢህአደግ አመራር እንዳየመጣ ለመከላከል የተወሰደ እርምጃ ነው።
ጁነዲን ሳዶ በጳጉሜ ወር 2002 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ተካሄዶ በነበረው የኦህዴድ ስድስተኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ላይ በመተካካት ስም ከኦህዴድ እና ከኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚነት ከተሰናበቱት አስቴር ማሞ እና ሽፈራው ጃርሶ ጋር ከሥራ አስፈጻሚነት መነሳቱ ይታወሳል::

በአሁኑ ወቅት ኦህዴድን በኢህአዴግ ውስጥ የሚወክሉ የስራአስፈጻሚ አባላት አለማየሁ አቶምሳ ፤ ሙክታር ከድር፣ ግርማ ብሩ፣ አባዱላ ገመዳ፣ ኩማ ደመቅሳ፣ ሶፊያን አህመድ፣ ድሪባ ኩማና አብዱልአዚዝ አህመድ ሲሆኑ ዘላላም ጀማነህ ከዚህ ቀደም በሥነምግባር ችግር ተገምግሞ ከሥራ አስፈጻሚነት ቦታው ተነስተአል::

የፊታችን ህዳር ወር 2005 በሚካሄደው የኢሃደግ ድርጅታዊ ጉባዔ ላይ በሕመም ምክንያት መልቀቂያ ባቀረበው የፓርቲው ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳ ምትክ አዲስ ሊቀመንበር የሚመረጥ ሲሆን እንደ ጁነዲን ሳዶ በህወሃት ላይ ልባቸው የሸፈቱ ሌሎች ሰዎች ተለቅመው ከኃላፊነታቸው ሊነሱ እንደሚችሉ ምንጮች ይናገራሉ።

ጁኔድን ሳዶን ከነበረበት ስልጣንና ሃላፊነት የፈነገለውና የኦህዴድ "አመራሮችን ለአንድ ሳምንት ሲያተረማምስ የሰነበተው ግምገማ" በ2004 መገባደጃ አካባቢ በቦረናና በጋሪ ብሔረሰቦች መካከል ተፈጥሮ ለበርካታ ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው ግጭት በድርጅቱ አመራር ድክመት እንደተፈጠረ ተቆጥሮ እርምት እንዲደረግበት ዉሳኔ አሳልፏል።

እንደምንጫችን መረጃ የጨፌ ኦሮሚያ ም/ቤት መደበኛ ስብሰባውን ሲጀምር የጁነዲን ሳዶን የመከሰስ መብት መነሳቱን ያጸድቅና ከሳውዲ ኤምባሲ የተሰጣትን ገንዘብ ተረክባ ስተወጣ ተይዛ እስር ቤት ከተወረወረቺው ባሌበቱ ጋር በአባሪ ተባባሪነት እስር ቤት ሊወርድ እንደሚችል ይጠበቃል።
ወያኔ የአገራችንን ሃብትና ንብረት ለመዝረፍ በመሳሪያነት የሚጠቀምባቸው የሌላ ብሄረሰብ ተወላጆች ከጁነዲን ሳዶ አይነቶቹ ሊማሩ የሚገባው ትምህርት ሳይቀደሙ ከህዝባቸው ጋር በመወገን ተራ በተራ ተዋርደው እስር ቤት ከመወርወር እራሳቸውን እንዲያድኑና በአገራችን ፍትህ ለማስፈን የሚደረገውን ትግል እንዲቀላቀሉ ነው።

## በእስራኤል የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ያደረጉትን ስብሰባ ለማደናቀፍ የሞከሩ የወያኔ ደጋፊዎች በውርደት ከአዳራሹ መባረራቸው ተዘገበ

በእስራኤል ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በወቅታዊ የሀገራቸው ሁኔታ ላይ እየተወያዩ ባሉበት ስብሰባ ላይ ተመሳስለው ገብተው የስብሰባውን መንፈስ ለማወክ የሞከሩ የወያኔ ተላላኪዎች በተሰብሳቢዎቹ ተቃውሞ በፖሊስ ከአዳራሹ እየተጎተቱ እንዲወጡ መደረጋቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ከስብሰባው አካባቢ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በህዝባችን ላይ የሚደርሰው መከራና ሲቃይ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ለወያኔ በማደር በሚገኝ ርካሽ ጥቅም የታወሩ እነዚህ የወያኔ ተላላኪዎች ከአዳራሹ እየተጎተቱ ሲወጡ ከተሰብሳቢዎቹ በከፍተኛ ቁጣ የታጀበ "ወያኔ ሌባ" የሚል መፈክር ተደምጧል።

የስብሰባው አስተባባሪ በበኩላቸው እነዚህ ሰዎች በስብሰባው በመሳተፍ እንደ ሰው በስነስርዓት የፈለጉትን ሀሳብ እንዲያራምዱ የተቻላቸውን ሁሉ ጥረው እንደነበር በመግለጽ በተለመደው ባህሪያቸው ምክንያት ባለመሰካቱ ቅር እንዳላቸው ገልጸዋል። በዚሁ ወቅት በስብሰባው ውስጥ ስርዓቱን ጠብቆ ከተካፈለው ክብሮም ከተባለው የወያኔ ደጋፊ "ለምን ሁልጊዜ ትቃወማላችሁ? አንዳንድ ጊዜ እንኳን ጥሩ ነገር ሲሰራ ለምን አታመሰግኑም?" የሚል ጥያቄ የተነሳ ሲሆን ከመድረኩ፣ ሲጀመር ወያኔ ምን ጥሩ ነገር አለውና ጥሩ ነው እንበለው? ከ37 ዓመት በፊት ጸንሶት የመጣውን ሀገር የማፍረስ ውጥን ለማሳካት እየሰራ ያለን ድርጅት እንዴት እናመስግን? የ 3 ሺህ ብር ደሞዝተኛ ጄነራሎች ከ45 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው ህንጻዎች ባለቤቶች የሆኑባትን ሀገር የፈጠረ ስርዓት እንደምን ጥሩ ነው ብለን እንመስክር?ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥሩ ነገር ቢኖር ኖሮ እዚህ ምን እናደርጋለን?ሌላው ቢቀር ሽብርተኛ በሚል በግፍ ያሰራቸውን ዜጎች እንኳን ነጻ ለማድረግ ሃሳቡ እንኳን ለሌለውን ስርዓት እንደምን ጥሩ ሰርቷል ብሎ እማኝ መስጠት ይቻላል የሚል ምላሽ ተሰጥቶታል።

በስብሰባው ላይ የተገኙት የሃይማኖት አባትም እንዲሁ ለዘረኞቹ የወያኔ ገዢዎች መልእክት ማስተላለፍ እንፈልጋለን በማለት "የንጹሃን ደም ማፈሰስ ይብቃ!" "የህዝብ ህይወት መቅጠፍ ይቁም!" "የህዝባችን የመከራ ዘመን ያብቃ!" ማለታቸው ታውቆአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org